47ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት ዶናልድ ትራምፕ ቃለ መሐላ በፈጸሙበት ወቅት ያደረጉት ንግግር።

ትርጉም ፡አቤል ጋሼ

አመሰግናለሁ። እያንዳንዱን ሰው በጣም እጅጉን አመሰግናለሁ። በጣም በጣም እጅጉን አመሰግናለሁ። ምክትል ፕሬዚዳንት ቫንስ። አፈ ጉባኤ ጆንሰን። ሴኔተር ትሁን። ዋና ፈታሒ ሮበርት። የተባበሩት ግዛቶች የታላቁ ፍርድ ቤት ፈታሕያን። ፕሬዚዳንት ክሊንቶን። ፕሬዚዳንት ቡሽ። ፕሬዚዳንት አባማ። ፕሬዚዳንት ባይደን። ምክትል ፕሬዚዳንት ሃሪስ። እና ወገኖቼ የሀገሬ ነዋሪዎች።

ወርቃማው የአሜሪካ ዘመን አሁን ይጀምራል።

ከዛሬ ቀን ጀምሮ ሀገራችን እንደገና የምታንሠራራ ሲሆን በአለም ዙሪያ እንደገና ትከበራለች። ወደፊት እያንዳንዱ ሀገር እኛን መሆን የሚመኝ ሲሆን ከዚህ በኋላ ማንም በእኛ ላይ አላግባብ እንዲጠቀምብን አንፈቅድም። በእያንዳንዷ የትራምፕ አስተዳደር ቀን ውስጥ አሜሪካን ከሁሉም በፊት አንደኛ አደርጋለሁ።

ሉዓላዊነታችንን እንደገና ይረጋገጣል። የደኅንነት ዋስትናችንን እናስመልሳለን። የፍትሕን ሚዛናዊነቶች እንደገና እናመጣጥናለን። የፍትሕ አስተዳደር ክፍላችንና መንግሥታችን ጨካኝ፣ ጉልበተኛና፣ አድልዎ በተመላው መንገድ የጥቅም ማስፈጸሚያ መሳሪያ መሆኑ ያበቃል። ዋና ተቀዳሚ አጀንዳችን የሚሆነውም የበለጸገ ነጻና ኩሩ ሀገር መፍጠር ነው። አሜሪካ በቅርቡ የበለጠ፣ የጠነከረና ከአሁን በፊት ከነበረው በጣም በበለጠው የተለየ ይሆናል።

ወደ ፕሬዚዳንትነቱ የምመለሰው አዲስ ብሔራዊ ድሎችን ለማስመዝገብ በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ ተስፈኛ በመሆንና በልዕልና መንፈስ ነው። የለውጥ ማዕበል ሀገሩን እየጠረጋት ነው፤ የለውጥ ፀሀይ ብርሃን ውጋጋን በአለም ዙሪያ እየታየ ነው። አሜሪካም ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ይኸንን እድል የመጠቀም አጋጣሚ አግኝታለች። ሆኖም ግን በመጀመሪያ ከፊታችን ተደቅነው ስላሉ ተግዳሮቶች ሐቀኛ መሆን ይኖርብናል። ምንም እንኳን ብዙ ቢሆኑም አለም ዛሬ ምስክር ሆኖ በሚያየው በተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች ውስጥ በሚታየው ታላቅ የለውጥ አየር ተግዳሮቶች ሁሉ ይደመሰሳሉ።

ዛሬ እዚህ እኛ በተሰበሰብንበት በአሁኑ ወቅት መንግሥታችን ከፍተኛ የሆነ የአመኔታ ቀውስ አጋጥሞታል። የማኅበረሰባችን ዋልታዎች ተሰባብረውና በጠቅላላ ከጥቅም ውጭ ሆነው እየታዩ ለብዙ አመታት አከራሪና ሙሰኛ የሆነው ተቋም ከዜጎቻችን ሥልጣንና ሐብት መዝምዟል። አሁን ያለን መንግሥታችን ከሀገር ውጭ በብዙ የሚዘረዘሩ የጥፋት ሁነቶች ውስጥ እየገባ እየተደነቃቀፈ እየታየ ነገር ግን እዚሁ ሀገር ውስጥ ግን ጥቃቅን ችግሮችን እንኳ በትክክል መፍታት የተቸገረበት ጊዜ ላይ ነው። ህግ

DONALD TRUMP SPEECH

47ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት ዶናልድ ትራምፕ ቃለ መሐላ በፈጸሙበት ወቅት ያደረጉት ንግግር

ትርጉም፡ አቤል ጋሼ

አከባቢ የሆኑ ድንቅ አሜሪካዊ ዜጎቻችንን መከላከል ሳይችል፣ ግን አደገኛ ለሆኑ ይልቁንም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ከአለም ዙሪያ ወደ ሀገራችን የገቡ ብዙዎቹ ከእሥር ቤቶችና ከአእምሮ ሕሙማን ተቋማት ለመጡ ወንጀለኞች መደበቂያ ሆኗል።

አሁን ያለን መንግሥት ጐልቆ መስፈርት የሌለው የገንዘብ እርዳታ እየሰጠ የውጭ ድንበሮችን የሚከላከል ሲሆን ግን የአሜሪካን ድንበር ፣ ይልቁንም የራሱን ሕዝብ ለመከላከል ፈቃደኛ ያልሆነ ነው። ሀገራችን በአደጋ ወቅት መሠረታዊ አገልግሎቶችን ማቅረብ የማትችል መሆኑን በቅርቡ በሰሜን ካሮላይና መልካም ሕዝብ ላይ የሆነውን አይተናል። የሆነባቸው ነገር በጣም ክፉኛ ነው። ከወራት በፊት የአውሎ ነፋስ የደረሰባቸው ሌሎች ግዛቶችም እስካሁን ድረስ እየተቸገሩ ነው።

ወይም በቅርቡ በሎስ አንጀለስ እንደምናየው እስካሁን እሳት በሚያሳዝን ሁኔታ እየነደደ ነው። ከሳምንታት በፊት የጀመረው እሳት ምንም አይነት ስንጥር መከላከያ በሌለበት ሁኔታ ዛሬም እሳቱ በቤቶችና በማህበረሰቡ ውስጥ የእሳት ቋያዎች እየተንቀለቀሉ ይታያል፤ እንዲያውም በሀገራችን በጣም ኃብታም የሚባሉትንና በጣም ኃያላን ግለሰቦችን ሁሉ ያዳረሰ ነው። አንዳንዶቹም ዛሬ እዚህ አሁን ተቀምጠዋል። በቃ ምንም ቤት የላቸውም። የሚገርም ነው።

ይኸ ግን እንዲሆን አንፈቅድም። ማንም ምንም ማድረግ አልቻለም።. ያ ግን መለወጥ አለበት። ያለን የሕዝብ ጤና አጠባበቅ ሥርዓት በአለም ላይ ከማንኛውም ሀገር በበለጠ ገንዘብ የሚወጣበት ይሁን እንጅ በከፍተኛ የጥፋት አደጋ በተደቀነ ጊዜ የተጠበቀውን አገልግሎት መስጠት የማይችል ነው። ምንም እንኳን ለልጆቻችን ፍቅርን ሰጥተን ለማሳደግ እየተፍጨረጨርን ብንሞክርም ልጆቻችን የሚማሩበት የትምህርት ሥርዓት በብዙ መልኩ በራሳቸው እንዲያፍሩርና ሀገራችውን እንዲጠሉ የሚያደርግ ነው። ይኽ ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ የሚለወጥ ሲሆን፣ በጣም በፍጥነትም ይለወጣል።

በቅርቡ በተደረገው ምርጫ ማሸነፌ በጠቅላላና ሁሉንም አሳዛኝ ክህደቶችና የክህደት ሂደቶች ለመገልበጥና ለመቀየር የተሰጠኝ ሙሉ ይሁንታ ፈቃድ ሲሆን አላማውም ለሕዝቡ መልሶ እምነቱን ሀብቱን ዲሞክራሲን ብሎም ነጻነቱን መመለስ ነው። ከዚች ቅጽበት በኋላ የአሜሪካ ማሸቆልቆል ያበቃል።

የነጻነታችንና የሀገራችን ታላቅ አላማዊ ዕጣ የሚከለከል አይሆንም። ወዲያውኑ የአሜሪካን መንግሥት ሐቀኛነት፣ ብቃትና፣ ታማኝነት በቦታው እንመልሳለን።

ባለፉት ስምንት አመታት ባለፉት 250 አመታት ታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ ከሌሎች ፕሬዚዳንቶች በበለጠ ተፈትኛለሁ፣ ተግዳሮቶችም አጋጥመውኛል። በዚህ ጉዞዬም ውስጥ ብዙ ተምሬያለሁ። ሪፓብሊካችንን እንደገና ለማጽናት የሚደረገው ጉዞ ግን ቀላል እንዳልሆነ ልነግራችሁ እወዳለሁ። አጀንዳችንን ማስቆም የፈለጉ አካላት ነጻነቴን ለመውሰድ ሞክረዋል፣ አንዲያውም ሕይወቴንም ጭምር ለማጥፋት።

አሁን ከጥቂት ወራት በፊት እዚያ በሚያምር የፔንስልቫንያ ሜዳ የገዳይ ጥይት ጆሮዬን በስቶኛል። ያኔም እንደተሰማኝ፣ እንዲያውም አሁን በበለጠ እንደማምነው ሕይወቴ የተረፈው ለምክንያት ነው። አሜሪካን እንደገና ለማትረፍ ያተረፈኝም እግዚአብሔር ነው።

ለዚያም ነው በእያንዳንዱ ቀን በአሜሪካዊ የአርበኝነት መንፈስ በሚታነጸው አስተዳደራችን ውስጥ እያንዳንዱን ተግዳሮት መፍትሄ ለመስጠት በክብር፣ በኃይልና በጥንካሬ የምንሠራው።። እንቅስቃሴያንን በአላማና በፍጥነት በማድረግ ከሁሉም ዘር፣ ኃይማኖት፣ ቀለም እምነት ለሆኑት ለሁሉም ዜጎቻችን ሰላምንና ደኅንነትን ለማምጣት እንንቀሳቀሳለን። ለአሜሪካ ዜጎች ጃኑዋሪ 20 2025 የነጻነት ቀን ነው።

በቅርቡ ያደረግነው የፕሬዚዳንት ምርጫ ከምንጊዜውም በላይ የበለጠና ከዚህ በፊት ያልታዩ ክንዋኔዎችን የሚያስከትል መሆኑን በሀገራችን ታሪክ እንደሚታወስ ተስፋ አደርጋለሁ። ድላችን እንደሚያመላክተው ጠቅላላ ሀገሩ በአጀንዳችን ዙሪያ በአንድነት እየተሰለፈ ይገኛል፤ በተለይም ከሁሉም የሀገሪቱ የኅብረተሰብ ክፍል በሚገርም ቁጥር እየጨመረ የመጣ ድጋፍ፡ ወጣትና አሮጊት፣ ሴቶችና ወንዶች፣ አፍሪካ አሜሪካውያን፣ ሂስፓኒክ አሜሪካውያን፣ እስያዊ አሜሪካውያን፣ መሀል ከተማዎችንና፣ ከተማዎቻችን ብሎም ከገጠሩ ክፍል አግኝተናል። ይልቁንም በጣም ጠቃሚውና በከፍተኛ ቁጥር ያሸነፍነው በሰባቱም ተለዋዋጭ ገጽታ ባላቸው ሰባት ግዛቶች ሲሆን የሕዝቡንም ተቆጣሪ ድምጽ በሚሊዮኖች አሸንፈናል።

ለጥቁሩና ለሂስፓኒክ ማህበረሰብ በሙሉ የምርጫ ድምጻችሁን ለኔ በመስጠት ላሳያችሁኝ የላቀ ድጋፍና ላሳያችሁኝ ፍቅርና አመኔታ ማመስገን እፈልጋለሁ። በዚህ ደግሞ ከዚህ በፊት ያልታየ ውጤት ስላስመዘገብን የምረሳው አይደለም። በምርጫው ዘመቻ ወቅት ድምጻችሁን ሰምቻለሁ፤ በመሆኑም በመጪዎች አመታት አብሬያችሁ ለመሥራት ተዘጋጅቻለሁ። ዛሬ የማሪቲን ሉተር ኪንግ ቀንና የክብሩ ቀን ነው፤ ይህም ትልቅ ክብር ነው። ለሱም ክብር አብረን በመሥራት የሱን ህልም እውን እናደርጋለን። የሱን ሕልም እውን እንዲሆን እናደርጋለን።

ብሔራው አንድነት ወደ አሜሪካ እየተመለሰ ነው። በራስ መተማመንና በራስ መኩራት ከምንጊዜውም በላይ እያንሰራራ ይገኛል። በምንሠራው ሁሉ የኔ አስተዳደር ጠንካራ የሆነ የውጤታማነትን አጀንዳ ለማራመድና ከፍተኛ ውጤታማነትን ለማስመዝገብ የምንነቃ ሲሆን ሀገራችንን አንረሳም፤ ሕገ መንግስታችንን አንረሳም፤ እናም እግዚአብሔርን አንረሳም። ይኽንን ልናደርግ አንችልም።

ዛሬ ታሪካዊ የሆኑ ተከታታይ የሥራ አስፈጻሚ ትዕዛዛትን እፈርማለሁ ። እነዚህን ታሪካዊ የሥራ አፈጻጸም ትዕዛዛትን በመፈረም የአሜሪካን እንደገና በክብሩ የማቆም ሥራና ተፈጥሮአዊ የጋራ እሳቤዎችን አብዮት እንጀምራለን። ሁሉም ነገር ተፈጥሮአዊ ስለሆኑ የጋራ እሳቤዎች ነው።

በመጀመሪያ በደቡብ በኩል ስላለው ድንበራችን ብሔራዊ የአደጋ ጊዜ አውጃለሁ። ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ መግባት ወዲያውኑ አሁን እንዲቆም ይደረጋል። ሚሊዮኖችና ሚሊዮኖች የሚሆኑ ወንጀለኛ የውጭ ስደተኞችን ወደመጡባቸው ቦታዎች የመመለሱን ሂደት እንጀምራለን። “ሜክሲኮ ውስጥ ቆይ” የሚለውን ፖሊሲዬን እንደገና ወደ ሥራ እንመልሳለን። ይዞ መልቀቅ የሚል የድርጊት አካሄድ አቆማለሁ። ሀገራችንን ላይ እየተፈጸመ ያለውን አጥፊ ወረራ ለመከላከል ወደ ደቡብ ድንበራችን ወታደሮችን እልካለሁ።

ዛሬ በፈረምኳቸው ት ዕዛዛት የውጭ ካርቴል ድርጅቶችን እንደ አሸባሪ ድርጅቶች እፈርጃቸዋለሁ። የ1978 የውጭ ጠላቶችን ያማከለ ሕገ ውሳኔን ወደ ሥራ በማምጣት መንግሥታችን የሀገሪቱን የፌዴራልና የግዛት ሕጎችን ሙሉ ኃይልና ጉልበት በሥራ ላይ በማዋል በከተማዎቻችንና በዙሪያቸው ባሉ ከተሞች ከፍተኛ ጥፋት የሚያስከትሉ የወንጀል ድርጊቶችን ለመፈጸም ወደ አሜሪካ ምድር የሚያመጡ በሀገራችን የሚገኙ የውጭ ጉልበተኛና የወመኔ የወንጀል ሰንሰለታማ መረቦችን እንዲያጠፉ አዝዛለሁ።

47ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት ዶናልድ ትራምፕ ቃለ መሐላ በፈጸሙበት ወቅት ያደረጉት ንግግር

ትርጉም፡ አቤል ጋሼ

እንደ ሀገሪቱ የጦር ኃይሎች አለቃ ሀገራችንን ከጥፋትና ከወረራ ከመከላከል የበለጠ ኃላፊነት የለኝም። ይሽንኑም ነው በእርግጠኝነት የማደርገው። ከዚህ በፊት ማንም አይቶት በማያውቅ ሁኔታ እናደርገዋለን። በመቀጠልም የካቢኔዬ አባላት የሆኑትን ሁሉ ያላቸውን ሁሉ ሥልጣን ተጠቅመው ከልክ ያለፈ የዋጋ ግሽበት በመዋጋት ወጪንና ዋጋን እንዲቀንሱ አዛለሁ። የዋጋ ግሽበት የተፈጠረበት ምክንያት ከአቅም በላይ ወጪ በማውጣትን እየናረ የመጣው የኃይል ዋጋዎች ነው። ለዚያም ነው ዛሬ የብሔራዊ የኃይል ቀውስ እንዳለ የማውጀው። ነዳጅ እናወጣለን፤ አ ስኬት ! እናወጣለን።

አሜሪካ እንደገና አምራች ሀገር ትሆናለች። እናም ሌላ አምራች ሀገር ምንጊዜም ሊኖረው የማይችለው ነገር አለን፤ ይሽውም በምድር ላይ ከሚገኝ ማንኛውም ሀገር ካለው ከሁሉም የሚበልጥ የዘይትና ጋዝ ተቀማጭ አለን፤ እናም እሱን እንጠቀምበታለን። ዋጋዎችን እንቀንሳለን፤ የስትራቴጅ መጠባበቂያችንን እንሞላዋለን፣ እስከ ከፍተኛው ደረጃው ድረስ እንሞላዋለን፤ የአሜሪካን የነዳጅ ኃይል በአለም ዙሪያ እንሸጣለን።

እንደገና ሀብታም ሀገር እንሆናለን፤ ይሽንንም ለማድረግ የሚረዳን ከእግራችን ሥር ያለው ወርቃማ ፈሳሽ ነው። ዛሬ በምወስዳቸው እርምጃዎች የአረንጓዴው አዲስ ውል የሚባለውን በማስቆም የኤሌክትሪክ መኪናዎች ግዴታነቱን እንሰርዛለን። ይህን በማድረግም የመኪና ኢንዱስትሪያችንን የምንታደግ ሲሆን ለገናናዎቹ የአሜሪካ የሞተር መኪና ሰራተኞች የገባሁላቸውን ክቡር ቃል ኪዳን አከብራለሁ። በሌላ አነጋገር የምትመርጡትን መኪና መግዛት ትችላላችሁ። በአሜሪካ ውስጥ እንደገና ከቅርብ አመታት በፊት ማንም ሊያልመው በማይችለው ደረጃ ዋጋቸው የቀነሱ መኪናዎችን መሥራት እንችላለን። እናም የሀገራችንን መኪና አምራች ሠራተኞች በእኔ ላይ ያላችሁን አመኔታ የሚገልጽ የምርጫ ድምጻችሁን ስለሰጣችሁኝ አመሰግናችኋለሁ። በሰጣችሁን ድምጽ የላቀ ውጤት አስመዝግበናል።

የሀገራችንን የንግድ ሥርዓት እንደገና በሙሉ ለማሻሻል የአሜሪካን ሰራተኞችን ቤተሰቦች ለመከላከል የሚያስችል እርምጃ አሁኑኑ እጀምራለሁ። የራሳችንን ዜጎች ታክስ እያደረግን የውጭ ሀገራትን በማበልጸግ ፋንታ፣ ከውጭ ሀገራት ታሪፍና ታክስ በመሰብሰብ የራሳችንን ዜጎች እናበለጽጋለን። ለዚህ አላማ የውጭ ገቢዎች አገልግሎት አቋቁመን ታሪፍና ግዴታዎች ብሎም የቀረጥ ገቢዎችን እንሰበስባለን። በዚህም ምክንያት ይህም በጣም በርካታ የሆነ ገንዘብ ከውጭ ምንጮች ወደ ገንዘብ ቤታችን እንዲገባ ያደርጋል።

የአሜሪካ ህልም እንደገና ተመልሶ ከዚህ በፊት ሆኖ ከሚያውቀው በተለየ የሚንሰራራ ይሆናል። በመንግሥታችን ውስጥ ብቃትንና ውጤታማነትን እንደገና በሚገባው ደረጃ ለመመለስ በአይነቱ አዲስ የሆነ የመንግሥት ቅልጥፍና መምሪያ እናቋቁማለን።

በነጻነት የመናገርን መብት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድና ሕገ መንግስታዊነት በሌለው አካሄድ ለመወሰን ለአመታትና ለአመታት ከተደረገ የፌዴራል ጥረቶች በኋላ ማንኛውንም የመንግሥት ሳንሱር የሚያስቆምና በአሜሪካ በነጻነት የመናገርን መብት የሚመልስ የሥራ ማስፈጸሚያ ትእዛዝ እፈርማለሁ።

ከዚህ በኋላ በጣም የነለበተውን የግዛት አስተዳደርን ኃይል መሳሪያ በማድረግ የፖለቲካ ተወዳዳሪዎችን ማሳደድ አይቻልም፣ ስለዚህም ነገር የማውቀው ጉዳይ ነው። ይህ እንዲሆን አንፈቅድም። እንደገናም ወደፊትም አይሆንም። በኔ አመራር በሕገ መንግስቱ ህግጋት ውስጥ የታቀፈ ሚዛናዊ የሆነ፣ በእኩልነትና አድልዎ በሌለው ሁኔታ የተመሠረተ ፍትሕ እንዲኖር እናደርጋለን። ህግና ሥርዓትም በከተሞቻችን እንደገና እንዲሰፍን እናደርጋለን።

DONALD TRUMP SPEECH

47ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት ዶናልድ ትራምፕ ቃለ መሐላ በፈጸሙበት ወቅት ያደረጉት ንግግር

ትርጉም፡ አቤል ጋሼ

ዘርንና ጾታን በእያንዳንዱ የአሜሪካ ሕዝባዊም ይሁን የግል ሕይወት ውስጥ በማህበራዊ ቀመር ለመፐወዝ የሚደረገውን የመንግሥት ፖሊሲ ሙከራ እንዲሁ በዚህ ሳምንት አስቆማለሁ። ቀለምን የማይመልከት በክሂሎት ላይ የተመሠረተ ማኅበረሰብ እናዳብራለን። ከዛሬ ጀምሮ ከዚህ በኋላ የተባበሩት ግዛቶች መንግሥት የታወቀ ፖሊሲ የሚሆነው ሁለት ጾታዎች ብቻ መኖራቸውን ነው። ወንድና ሴት።

በ 2017 እንደሆነው አለም ከአሁን በፊት አይቶት የማያውቅ ከሁሉም የሚጠነክር ሚሊታሪ እንገነባለን። ውጤታማነታችንን የምንለካው ባሸነፍናቸው ጦርነቶች ብቻ ሳይሆን ባቆምናቸው ጦርነቶችም ጭምር ይሆናል ምናልባትም እንዲያውም በጣም ጠቃሚው ባልገባንባቸው ጦርነቶች ይሆናል።

የኔ እጅጉን የምኮራበት ቅርሴ የሚሆነው ሰላምን የማመጣና ሁሉንም ወደ አንድነት በማምጣቴ ይሆናል። ደስ ብሎኝ የምናገረው ክትላንትና ጀምሮ፣ አንድ ቀን የቢሮ ኃላፊነት ከመጀመሬ በፊት በመካከለኛው ምሥራቅ የታገቱት ወደ ቤታቸው ብሎም ወደ ቤተሰቦቻቸው እየመጡ ነው። አመሰግናለሁ።

አሜሪካ በጠቅላላ በምድር ላይ ወደር የሌላት ታላቅ ሀይለኛና ለሁሉም ማነቃቂያ የምትሆን ከሁሉም በላይ የተከበረችና የምታስደንቅ ሀገር በመሆን ትክክለኛ ቦታዋን ትይዛለች። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሜክሲኮ ሰላጤ የሚባለውን ስም ቀይረን የአሜሪካ ሰላጤ እንለዋለን። የታላቁን ፕሬዚዳንት ስም ወደ ነበረበት ክብሩ እንመልሰዋለን፤ ዊሊያም መኪንሊይ የሚለውን ውደ ማውንት መኪንሊይ፣ ወደነበረበትና ወደሚገባው ቦታው እንመልሰዋለን።

ፕሬዚዳንት መኪንሊይ ሀገራችንን በታሪፍና በተሰጥኦ በጣም ሀብታም ያደረገ ነው። በተፈጥሮው የንግድ ክሂሎት የነበረው ሲሆን ለፕሬዚዳንት ቴዲ ሩዝቨልት ብዙ ታላላቅ ነገሮችን እንዲያደርግ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ይሰጠው ነበር፣ የፓናማ ካናልንም ጨምሮ፣ ያው የቂልነት ጉዳይ ሆኖ ከተባበሩት ግዛቶች ፓናማ ለምትባል ሀገር ተሰጠ። የተባበሩት ግዛቶች - ማለቴ እስኪ አስቡት - የፓናማ ካናልን ለመገንባት ከዚህ በፊት ለሌላ ፕሮጀክት ወጭ ሆኖ ከሚያውቀው ሁሉ ገንዘብ ወጥቶበታል፤ 38000 ነፍሳት ጠፍተውበታል። ከዚህ መደረግ ከሌለበት የቂልነት ስጦታ በጣም የሚጎዳ ሁኔታ ነው የተድረገብን። ፓናማም የገባችልን ቃልኪዳንም ተሰብሯል። ቃል ኪዳን የገባንበት አላማም ይሁን የውላችን መንፈስ በጠቅላላው ተጥሷል።

የአሜሪካ መርከቦች በምንም መለኪያ ይሁን በቅርጽም ይሁን በአይነቱ ከፍተኛ ዋጋ እየከፈሉ ነው። ይሽም የአሜሪካን የባሕር ኃይል ያካትታል። ከሁሉም በላይ ቻይና የፓናማ ካናልን እያስተዳደረችው ትገኛለች። እኛ ለቻይና አልሰጠንም፤ የሰጠን ለፓናማ ነው። እናም መልሰን እንወስደዋለን።

ከሁሉም በላይ ዛሬ ለአሜሪካውያን ያለኝ መልእክት በታሪክ ወደር የሌለው ታላቁ ሥልጣኔን በሚመጥን ደረጃ እንደገና ከድፍረት፣ ከጉልበትና ከህያውነት ወደ ተግባር የምንሰማራበት ጊዜው አሁን ነው። ሀገራችንንም ነጻ ለማውጣት እንደገና ወደ አዲስ ከፍታና የአሸናፊነት ስኬት እንመራታለን። የሚገታን አይኖርም። አብረን በመሆን የሚስፋፉ ሥር የሰደዱ በሽታዎችን እናጠፋለን፤ እናም ልጆቻችንን ከበሽታ ነጻ የሆኑ ጤነኞችና ደኅንነታቸው የተጠበቀ እናደርጋለን።

አሜሪካ እንደገና ራሷን የምታድግ ሀገር አድርጋ ትቆጥራለች፤ ይህም ሀብታችንን የሚጨምር፣ የቦታ ይዞታችንን የሚጨምር፣ ከተማዎቻችንን የሚገነባ፣ ልንጎናጸፍ የምንፈልገውን ነገር ግምታችንን ከፍ የሚያደርግና ባንዲራችንን ውብ ወደሆነ አዲስ የህልውና አድማስና ከፍታ ይዘን እንድንገሰግስ የሚያደርገን ይሆናል።

በግልጽ የሚታየውን የህልውና ዕጣችንን ወደ ከዋክብት አለም እናመላክታለን፤ በዚህም የአሜሪካ አስትሮኖቶች (ኮከቦችና መስመሮች የተነሰነሱበትን)ባንዲራችንን ፕላኔት ማርስ ላይ ይተክሉታል።

ተነሳሽነትን የአንድ ታላቅ ሀገር የሕይወት ደም ነው። በአሁኑ ጊዜ ሀገራችን ከማንም ሌላ ሀገር በበለጠ ተነሳሽ ነች። እንደኛ ሀገር ያለ ሌላ የለም፡፤ አሜሪካውያን አዲስ ነገር ፈላጊዎች፣ ገንቢዎች፣ ፈጣሪዎች፣ ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዲስ ራእይ አፍላቂዎች ናቸው። የፈር ቀዳጅነት መንፈስ በልባችን የተጻፈ ነው። የሚቀጥለው አዲስ ግኝት ጥሪ በነፍሳችን ውስጠት ውስጥ ሲያቃጭል ይሰማል። አሜሪካዊ ቅድመ አያቶቻችን በአንድ ግዙፍ አህጉር ጫፍ ላይ የሚገኙ ጥቂት የነበሩ ቅኝ ግዛቶችን ወስደው በምድር ላይ እጅግ በጣም የተለዩ ዜጎች የሚኖሩበት ወደ አንድ ታላቅ ሬፑብሊክ ቀይረዋል። ማንም ወደዚህ ሊጠጋ የሚችል የለም።

አሜሪካኖች በሺዎች ማይል የሚቆጠር ከዚህ በፊት ሰው ያልነካካው ድንግል መሬት መንጥረው ግዛት አስፍተዋል። በረሀዎችን አቋርጠዋል። ተራራዎችን ተወጣጥተዋል፤ አደገኛ የሆኑ ነገሮችን በድፍረት ተጋፍጠዋል፤ ኢሕጋዊ የነበረውን የምዕራቡን ክፍል አሸንፈዋል፤ ባርነትን አስቁመዋል፤ ሚሊዮኖችን ከክፉ የአገዛዝ ቀንበር አላቀዋል፤ ቢሊዮኖችን ከድህነት አላቀዋል፤ የኤሌክትሪክን ኃይል ፈጥረዋል፤ አቶምን ከፍለዋል፣ የሰው ልጅ ወደ ሰማያት አምጥቀዋል፤ ብሎም ጠቅላላ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ያለውን የሰውን እውቀት በሰው እጅ መዳፍ ላይ ማስቀመጥ ችለዋል። አብረን ከሠራን መሥራት የማንችለው ሥራ የለም፣ አልመን ልናሳካው የማንችለው ነገር አይኖርም።

ብዙ ሰዎች እንደገና ተመልሼ ታሪካዊ የሆነ የፖለቲካ ማንሰራራት ላሳይ የምችልበት መድረክ መፍጠር እንደማልችል አስበው ነበር። ዛሬ እዚህ እንደምታዩት ይኸው እዚህ ነኝ። የአሜሪካ ሕዝብ ተናግሯል።

ዛሬ ከፊታችሁ ስቆም እንደ ምሳሌ ልሆናችሁ የሚገባው ማንም ምንም ነገር ማድረግ አይቻልም ቢላችሁ በፍጹም ማመን የሌለባችሁ መሆኑን ነው። አሜሪካ ውስጥ ከሁሉም አብልጠን የምንሠራው ነገር ቢኖር የማይቻለውን ነው።

ከኒውዮርክ እስከ ሎስ አንጀለስ፣ ከፊላደልፊያ እስከ ፊኒክስ፣ ከቸካጎ እስከ ማያሚ፣ ከሂውስተን እስከዚህ እስካለንበት እስከ ዋሽንግቶን ዲሲ ሀገራችን የተቋቋመችውና የተገነባችው ለእኛ መብትና ለእኛ ነጻነት ሲሉ ሁሉን ነገራቸውን በሰጡ አርበኞች በሁኑ ትውልዶች ነው። እኒህም ገበሬዎችና ወታደሮች፣ ከብት አርቢዎችን የፋብሪካ ሠራተኞች፣ የብረት ሠራተኞችና ማዕድን ቆፋሪዎች፣ የፖሊስ ኦፊሰሮችና አዲስ ነገርን ለመፈለግ የሚታትሩ ክብራችውንም ይሁን መንፈሳቸውን የሚያሸንፍ ነገር እንዲኖር ሳይፈቅዱ ወደፊት የገሰገሱ ናቸው።

አብረው ሆነው የባቡር መንገዶችን ዘርግተዋል፤ ግዙፍ የሆኑ ፎቆችን አንጸዋል፤ ታላላቅ መገዶችን ሠርተዋል፤ ሁለት የአለም ጦርነቶችን አሸንፈዋል፤ ፋሺዝምና ኮሚኒዝምን አሸንፈዋል፤ የገጠማቸውን እያንዳንዱን ተግዳሮት ሁሉ በአሸናፊነት ተወጥተዋል። አብረን በዚህ ሁሉ ፈተና ውስጥ ካለፍን በኋላ በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ ወደር የሌላቸውን አራት አመታትን ከፊታችን አድርገን እንገኛለን። በእናንተ እርዳታ የአሜሪካን ቃልኪዳን እናድሳለን፣ ብሎም የምንወዳትን ሀገራችንን እንደገና እንሠራታለን፡፤ እናም ሀገራችንን በጣም እንወዳታለን።

እኛ አንድ ሕዝብ ነን፤ አንድ ቤተሰብ ነን፤ በእግዚአብሔር ሥር አንድ ታላቅ ሀገር ነን። ስለዚህም ስለልጁ ህልም የሚያልም ሁሉ፣ ብሎም ስለ መጪው ዘመን ህልም የሚያልም ልጅ ሁሉ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ።

ለእናንተ እታገላለሁ፣ ለእናንተ አሸንፋለሁ። ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኒታ እናሸንፋለን። አመሰግናለሁ፤ አመሰግናለሁ፤ አመሰግናለሁ።

በቅርብ አመታት ሀገራችን ብዙ ተጎድታለች። ግን እንደገና ወደ ክብሯ የምንመልሳትና ብሎም በበለጠ ከፍ የምናደርጋት ይሆናል፤ ከመቼውም ጊዜ በላይ የበለጠች እናደርጋታለን። ከማንም ሀገር ጋር የማትወዳደር ሀገር እናደርጋታለን፣ በርህራሄ የተመላች፣ ደፋርና ልዩ የሆነች ትሆናለች። ቁጡ በጸብ የተሞላና ምንም ሊገመት በማይችል ሁኔታ በሚታወቀው አለም ውስጥ ኃይላችን ሁሉንም ጦርነት ያስቆማል ፣ ብሎም አዲስ የአንድነት መንፈስ ያሰርጻል።

አሜሪካ በሁሉም ጎይማኖቶች፣ እምነቶችና በጎ ፈላጊዎች ዘንድ እንደገና ትከበራለች፤ እንደገናም ትደነቃለች። የበለጸግን እንሆናለን፣ የኮራን እንሆናለን፤ ጠንካራ እንሆናለን፤ ከዚህ በፊት በሌለ አይነት እንደገና እናሸንፋለን። አንወረርም፣ የሚያስፈራራን አይኖርም፣ አንሰበርም፣ አንወድቅም።፤ ከዛሬ ቀን ጀምሮ የተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች ነጻ፣ ሉዓላዊና ራሷን የቻለች ሀገር ትሆናለች።

በጀግንነት እንቆማለን፣ በኩራት እንቆማለን፤ በድፍረት እናልማለን፤ አሜሪካኖች ነንና ማንም ከፊታችን አይቆምም። የወደፊት ዕጣችን ከፊታችን ነው። ወርቃማው ዘመናችን ልክ አሁን ጀምሯል፤፡ አመሰግናለሁ። አሜሪካን እግዚአብሔር ይባርክ። ሁላችሁንም አመሰግናለሁ።

DONALD TRUMP SPEECH